ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

Coalition for Unity and Democracy Party
(Kinijit)

***ዜና ነክ መግለጫ፤ News Release:***

**በኢትየጵያ የህሊና እስረኞች ላይ የታሰበውን የካቲት 12 1999ቱን የፍትህ ቧልቲ አስመልክቶ፡፡**

***In relation to the coming Feb 19 2007 sham trial of prisoners of conscience in Ethiopia:***

**የከቲት 7 1999…** **ቁጥር 3**
February 14. 2007… NO **3**

# የሃገር ውጭ ዜና

## የሻማ ማብራት ስልፍ በአለም ዙሪያ

**በመላው አለም** የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በግፍ የታሰሩ የቅንጀት መሪዎችን ጋዜጠኞችን የሰብአዊና የዜጎች መብቶች ተሟጋቾችንና ሌሎችንም የህሊና እስረኞች ከወያኔ እስር ለማስፈታት ተከታታይ አለምአቀፍ የተቃውሞ ሰልፍ የሚያደርጉባቸው ቀናት እየተቃረቡ ነው፡፡ ለእዚህ ከነገ ከየካቲት 8 1999 አም ከሚጀምርው የሰልፍ ቀናት በፊት በተለያዩ ቦታዎች ሻማ በማብራት የሰላም፣ የእርቅና የተማጽኖ ጥሪ ፣ የተቃውሞና የትግል ቁርጠኛነት ማረጋጋጫ ትእይንተ ህዝቦች ተካሂደዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን በብዛት በሚገኙባቸው የአሜሪካ ዋና ከተሞች የካቲት 3 ና 4 1999 የሻማ መብራቱ የተካሄደ ሲሆን ከእዚህ ውጭ በሰኞ እለት የካቲት 5 1999 በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ቁጥራቸው ከስድስት መቶ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት በፕሪቶሪያ ከተማ ታላቅ የሻማ ማብራት ትእይንተ ህዝብ ተደርጓል፡፡ በዋሽንግተን ዲሲ በአሜሪካ ዋና ከተማ ቁጥራቸው በርካታ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት የሻማ ማብራት የተደረገ ሲሆን በሌሎችም የአሜሪካ ከተሞች በቦስተን፣ በሳውዝ ዳኮታ፣ በአትላንታ፣ በሎስአንጄለስ፣ በሚነሶታና በሌሎችም ቦታዎች ተመሳሳይ ትእይንቶች ተደርገዋል፡፡ በሁሉም ሻማ ማብራት በተደረገባቸው ቦታዎች የታየው የኢትዮጵያውያኑ ጽናትና ተሳትፎ፣ ኢትዮጵያውያኑን ወያኔ እንዳሰበው በማስፈራራት፣ በድለላና ለመከፋፈል በርካታ ገንዘብ በማጥፋት ባደረገው ሙከራ ትግላቸውን ያላቀዘቀዙ መሆናቸውን በተጨባጭ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በሁሉም ስፍራዎች አንዳንዴ ከዜሮ ዲግሪ በታች ብርድ በነበረባቸው ከተሞች ሳይቀር በተካሄደው ሰልፍ ላይ የነበረውን መንፈስ በሚመለከት ወይዘሮ አልጣሲ ሃሰን በዋሽንግተን ዲሲ የሻማ ማብራት ትእይንተ ህዝብ በላይ በመገኘት ስለራሳቸው ተሳትፎ ሲናገሩ «ለቆሙለት መሪዎቹ ያልቆመ፡ ለተሟገቱለት ያልተሟገተ ፣ ለተንገላቱለት ያልተንገላታ ህዝብ የመጨረሻው እድሉ መሪ አልባ መሆን ነው የሚል በራሪ ወረቀት ላካችሁልኝ፡፡ ይህ አባባል እንኳን እንደኔ ታሞ ካልጋ የወደቀን ቀርቶ የሞተን ከመቃብር ያስነሳል» ብለውታል፡፡ ወያኔ በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ትግል ይወድምልኛል ብሎ እንደተመኘው ሳይሆን ኢትዮጵያውያኑ ለእንቅስቃሲያቸው ያደረጃጀትና የአሰራር ብቃትና ጥራት ማላበስ በመቻላቸው በበርካታ ሃገሮች ትግላቸው የመገኛኛ ብዙሃናትን አይንና የመንግስታትን ትኩረት የሳበ ሆኗል፡፡ ከኢትዮጵያ ውጭ መለስ ዜናዊ እራሱንና ሃገሩን እያዋረደ በሎሌነት ለማደር ፈቃደኛነቱን ከሚያሳያቸው የውጭ ጥቂት መንግስታትና መሪዎች በስተቀር በሰው ልጆች ነጻነትና ዴሞክራሲ በሚያምኑ የአለም ዜጎች መንግስታትና ሀገራት ፊት የሚታወቀው በአስመሳይ ዴሞክራትነቱ ሳይሆን በለየለት ገዳይነቱና አፋኝነቱ እንዲሆን አድርገው እርቃኑን አስቀርተውታል፡፡ መለስ ዜናዊም ታሪክ በአጋጣሚ እጁ ላይ የጣለለትን ስልጣን ለሀገሩና ለወገኑ በጎ ነገር ሰርቶ በታሪክ መታወስ ሲችል ስልጣንና ከስልጣን የሚመጣን ተጠቃሚነት ጨብጦ ለመቀጠል ሲል እብሪትን ቋንቋው

አድርጎ እጣውን በአፍሪካ ምድር ተዋርደው እንዳለፉት አምባገነን ወንድሞቹ ከነሞቡቱ፣ ከነቦካሳ ከነመንግስቱ ሃይለማሪያም ጋር አቆራኝቶ አርፎታል::

## የአለም መገናኛ ብዙሃን በአለም አቀፉ የኢትዮጵያውያን አንቅስቃሴና ቃሊቲ በሚገኙ መሪዎች ላይ አተኩሯል::

ባለፈው ሳምንት ኢንዲፔንደንስ የተባለው የአንግሊዝ ጋዜጣ የመለስ ዜናዊን የለየለት አምባገናዊ ድርጊቶች ለምእራቡ አለም ህዝብ ማጋለጡን ዘግበን ነበር፡፤ ይህ በኢትዮጵያ ላይ ጋዜጣው ያሳየው ትኩረት በሌሎችም መገናኛ ብዙሃኖች እየተገለጸ ነው:: በበርካታ ቦታዎች ካጋዜጦች ራድዮኖችና ተሌቪዝን ጣቢያዎች የኢዮጵያውያኑን የሻማ ማብራት ትእይንተ ህዝብ ለየሃገራቸው ህዝብ ዘግበዋል:: የሻማ መብራቱ ሰልፍ በአትላንታ በቀጥታ ከቦታው ህያው የሆነ የቴሌቪዝን ሽፋን ሲያገኝ ፣ የዋሽንግተኑን ትእይንተ ህዝብ ወደ ሃገራችን በአማርኛ ቋንቋ በየቀኑ ስርጭት ያላቸው የአሜሪካና የጀርመን ድምጽ ራድዮ ጣቢያዎች ዘግበውታል:: የሳውዝ ዳኮታው ሰልፍ በህትመት መልኩ የተዘገበ ሲሆን ፣ በደቡብ አፍሪካ በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ድርጅት አማካይነት የተደረገውን ትእይንተ ህዝብ የታወቀው የደቡብ አፍሪካ የኤፍ ኤም ብሄራዊ ራዳዮ ከቦታው ዋና አዘጋጆቹን የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላትን ቃለመጠይቅ በማድረግ የደቡብ አፍሪቃ ህዝብ በኢትዮጵያ የሚካሄደውን የሰብአዊ መብት እረገጣ እንዲያውቅ አድርጎታል:: በደቡብ አፍሪቃ የተደረገው ሰልፍ ለደቡብ አፍሪካ ፕሬዚደንት ለአቶ ኢምቤኬ የተዘጋጀ ደብዳቤ ለጽህፈት ቤታቸው ሃላፊ ያስረከበ መሆኑ ተገልጧል:: በሌላ በኩልም በፌብሩዋሪ 12 የወጣው በኦስትርያ የሚገኘው ደርስታንዳረድ የተባለው ጋዜጣ የመለስ ዜናዊን አምባገነናዊ ድርጊቶች በአጠቃላይ በስፋት በመዘርዘር ለአንባቢዎቼ አቅርቧል:: ጋዜጣው ዛሬ በወያኔ እስርቤት ያለአግባብ ታስረው አበሳቸውን ስለሚያዩት የሀገሪቱ ብርቅየ ልጆች ማንነት ስማቸውን እየጠራ ዘርዝሮ በመግለጽ በኦስትርያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የወያን/ኢህአዴግን ግፍ በመኮነን በፌብሩዋሪ 15 ሰልፍ እንደሚደርጉ አትቷል:: ኔሽን የተባለው በአሜሪካ ሃገር የሚገኝ የድህረ ገጽ ጋዜጣ ከኢትዮጵያ የዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን አጠቃላይ አስተያየት ጭምር ባካተተው ሀተታው ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱና ነጻነቱን የአሜሪካኖች ጥቅም አስከባሪ ነኝ በሚል ግፈኛ አገዛዝ ተነጥቆ እንደሚኖር ተጨባጭ ማስረጃዎችን በማቅረብ ዘግቧል:: የቅንጅት የድጋፍ ደርጅቶች ፣ የቅንጅት አለም አመራርና ሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶችና ሃገር ወዳዶች ከቅርብ ግዜ ወዲህ የጀመሩት በእቅድ የሚመራ እንቅስቃሴ ለመገናኛ ብዙሃኑ ትኩረት መገኘት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳደረግ ታውቋል::

## የዲፕሎማሲና የሎቢ ግፊቱ ቀጥሏል::

ባለፈው የዜና ነክ መግለጫችን እንደገለጽነው በአውሮፓ የቅንጅትና የድጋፍ ድርጅቶችና የአለምአቀፍ ቅንጅት ትብብር ከጀርመን መንግስት ባለስልጣናት ጋር ይደረጋል የተባለው ውይይት ሰኞ የካቲት 4 1999 ተደርጓል:: ከጀርመን የፓርላማ አባላት ጋር ሰኞ ጠዋት የተደረገው ውይይት ከሁለት ሰአት በላይ የፈጀ ሲሆን በርካታ ጉዳዮችን በተለይ በቃሊቲ እና በሌሎች እስርቤቶች በግፍ ተይዘው የሚማቅቁትን የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ የሚመለከት ነበር:: ከፓርላማ አባለቱ ጋር የተደረገው ውይይት ከፍተኛ መግባባት የነበረው በመሆኑ ውይይቱ የተጠናቀቀው የፓርላማ አባለቱ የኢትዮጵያን የሰብአዊ መብት እረገጣ በሚመለከት መንግስታቸው ማድረግ የሚገባውን በመዘርዘርና ለእዚህና በተለይ በግፍ በወያኔ እስር ቤት የሚማቅቁትን የህሊና እስረኞች ለማስፈታት ተግተው እንደሚሰሩ ቃል በመግባት ነበር::

በእዚሁ እለት ከጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ባለስልጣናት ጋር የተደረገው ውይይት በአጠቃለይ የጀርመን መንግሰት በኢትዮጵያ ስለሚከተለው ፖሊሲ ከባለስልጣናቱ ገለጻ ተደርጓል:: በኢትየጵያና በአካባቢው ስላለውና ስለሚታየው የተወሳሰበ የፖለቲካ እውነታ ፣ በኢትዮጵያ ውስጥና ውጭ የሚገኙ ሃይሎች በሰላምና መረጋጋት በዴሞክራሲና በእድገት ጉዳዮች ላይ ሊኖራቸው ስለሚችለው አዎንታዊና አሉታዊ ተጽኖዎች በቅንጅት ተወካዮችና በጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለስልጣናት መሃል ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጓል:: በቅንጅት በኩል የካቲት 12 ወያኔ በእብሪት በፍትህ ስም የቅንጅት መሪዎችን እስራት ቢያራዝም በሃገሪቱ ውስጥ በቋፍ ያለው ሰላምና መረጋጋት አስከፊ ወደሆነ አዘቅት ሊያሽቆለቁል እንደሚችልና ይህም ከኢትዮጵያ አልፎ አካባቢውን ሊያናጋ እንደሚችል ሰፊ ገለጻ ተደርጓል:: የቅንጅት መሪዎች የአካባቢው የሰላምና የመረጋጋት ተስፈ እንደሆኑ፣ በአስቸኳይ ባይፈቱ ግን ሰላማዊና ህጋዊ ትግል አይቻልም በማለት ግፍና በደልን በአመጽ እንመክት ለሚሉት ወገኖች ለም መሬት እንደሚፈጠር ይህ ደግሞ አስፈሪ ወደ ሆነው የአልቂት አዙሪት እንደሚጨምረን፤ ዴሞክራሲ እድገት ደህና ሰንብቱ እንደሚባሉ በአጽንኦት በቅንጅት በኩል ተገልጧል:: በቅንጅት በኩል የቀረበው የኢትዮጵያ የወቅቱና የወደፊቱ የፖለቲካ ትንታኔ ህሊናቸውን የነካቸው

ባለስልጣናት የኢትዮጵያ ጉዳይ የተወሳሰበና የሚያስጨንቅ እንደሆነ በመጥቀስ «እናንተን አያድርገን» በሚል አባባል ራሳቸውን ገልጸው የጀርመን መንግስት ባሉት መስመሮችና አቅሙ እስከሚፈቅድለት ድርስ የሰብአው መብት ረገጣ በኢትዮጵያ እንዲቆም በፖለቲካ እምነታቸው የታሰሩ በመሉ ባሰቸኳይ እንዲፈቱ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል ቃል ገበተዋል:: «የዲፕሎማሲ ስራ በአደባባይ የሚታይ አለመሆኑ የምንሰራውን ማሰተዋወቅ አልቻልንም እንጅ በውስጥ በርካታ ጥረቶች እያደረግን እንደሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ሊረዳልን ይገባል» በማለት የጀርመን መንግስት በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ ለህግ የበላይነት ለመልካም አስተዳደር የሚያደርገውን ጥረት አለማቆሙን የጀርመኑ ባለስልጣን አበክረው ገልጸል::

በሌላ በኩልም ዋሽንግን ዲሲ ላይ በፌብሩዋሪ 15 በሚደረገወ ታላቅ ሰላመዊ ሰልፍ ላይ ለመገኘ ት በርካታ አፍሪካ አሜሪካዊ የኮንግረስ አባላት ከአትላነታ ድረስ በመኪና በጋራ በመምጣት ለአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ቢትዮጵያ ውስጥ ስለሚካሄደው የሰብአዊ መብት ረገጣ ያዘጋጁትን ሰነድ አንደሚሰጡ፤ መንግስታቸወም ኤች አር 5680 የሚባለውን በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ገፈፋ እንዲቆም ዴሞክራሲ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን የሚጠይቀውን የህግ ሀሳብ ህግ ሆኖ እንዲያወጣ ጥያቄ እንደሚያቀርቡ ተገልጧል:: አንዳንዶቹም በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ንግግር ያደርጋሉ:: የእነዚህን የአፍሪካ አሜሪካውያን ኮከስ ቡድን በመባል የሚታወቀውን የፖለቲካ ሃይል ድገፍ ማግኘት የተቻለው ቅንጅትና ሌሎችም ቢትየጵያውያን የሚመሩ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ድርጅቶች አትላንታ ላይ ተዋቁትን የጥቁር አሜሪካውያን መብት ተሟጋች የነበሩትን ማርቲን ሉተር ኪንግን የሙት አመት ለማክበር በተዘጋጀው በአል ላይ በመገኘት በሰሯቸው ስራዎችና በቀረቧቸው ገቀጻዎች አማካይነት ነው::

## *የሃገር ውስጥ ዜና*

### የፍትህ መዛባት የሰብአዊ መብት ገፈፈው ቀጥሏል::

በተለያዩ ምክንያት ታስረው የተፈቱ ግለሰቦች በሚሰጡት አስተያየት ከእስር ቤቱ አስከፊ ይዞታና በእስረኛው ላይ ከሚደርሰው የአካል ስቃይ ይበልጥ አሳሳቢ የሆነው የወያኔ ካድሬዎችና የጸጥታ ሃይሎች ዘረኛ የሆነ ስነልቦናን የሚያቆስል ንግግርና ስድብ ሆኗል:: ወያኔ በመንግስት ስር ሌላ ሙሉ በሙሉ በዘር የተደራጀ የአፈና□ የስለላ□ የገዳይና የደብዳቢ ቡድን ማደራጀቱ ከታወቀ የቆየ ቢሆንም እንዲህ አይነቱ አደረጃጀት አሁንም በስፋት እንደሚታየው ህዝብ ከህዝብ ሊያጫርስ የሚችል አደገኛ መርዝ እየዘራ ይቀጥላል ብለው ያሰቡ ጥቂቶች ነበሩ:: በምርጫው ወቅት ሰላምና እርቅን የሰበኩትን□ ዘረኛነትን የኮነኑትን የቅንጅት መሪዎች በኢነተር ሃሞይ ሲከስ የነበረው ወያኔ እራሱን በዘር አደራጅቶ ሰላማዊ ተቀዋሚዎቹን ለ□ሳ□ድ□ ለመግደልና ለማሰር ዘግጅት ሲያደርግ እንደነበር በተጨባጭ በግንቦቱና በጥቅምቱ ግድያና እስራት መለስ ዜናዊ እነማንን ታማኞች አድርጎ በገዳይነት በአሳሪነት በእስረኛ አመላላሽነትና ጠባቂነት እንዳስቀመጠ ግልጽ ነበር:: የመለስ ዜናዊ ቡድን እራሱ ዘረኛ በመሆን ዘረኛነት ተሰምቶት የማያውቀውን የኢትዮጵያ ህዝብ ዘረኛነት እንዲሰማው በሚያደርግ መንገድ የሚያኪሂደው አፈና□ ማዋረድና ማንገላታት የሚያሳየው መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ስልጣን ላይ እስከሌሉ ድረስ ህዝብ እርስ በርሱ ቢጫረስ ደም አንደጎርፍ ቢፈስ ደንታ የሌላችው መሆኑን ነው::

በሌላ በኩል በሃገራችን ነጻ ፍርድ ቤት ያለ ለማስመሰል በተለያዩ ችሎቶች ወያኔ ክስ መስርቶባቸው ከነበሩት የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች መሃከል ጥቂቶቹን ለቋል:: ከእነዚህ መሃከል የቅንጅተ መሪ የኤንጂነር ሃይሉ ጠበቃ የነበሬትን ያለምንም ማስረጃ ለአንድ አመት ለእስር የዳረጉትን አቶ ብርሀነ ሞገስን በአምስት ሽህ ብር ዋስ ፈቶ ለቋል:: ይህ የፍትህ ውሳኔ በጠቅላይ ሚኒስተሩ መኖሪያ ቤት ውስጥ ከብአዴን ሆድ አደሮች መሃከል አዲሱ ለገሰንና ተፈራ ዋልዋንና በረከት ሰምኦንንን በሌላ በከል ደግሞ ወያኔን ለመገየድ ከተጠጉ የወያነው ጋዜጣ የኢፍቲን አዘጋጆች ከነዘሪሁን ተሸመና የቀድሞዋ የትምህርት ሚኒስቴር የገነት ዘውዴ ወንድም ከገነነው አሰፋ ጋር በመመካከር የተወሰነ እንጂ ከፍርድ ቤቱ ሆነ ከዳኞቹ ውሳኔ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ለማወቅ ተችሏል:: እንዲህ የመሰለውን ከምኒልክ ቤተመንግስት በትእዛዝ የሚተላለፍን የመለስ ዜናዊና የግብረአበሮቹ ውሳኔ በግፍ በተከሰሱ የቅንጅት መሪዎችና ሌሎችም የህሊና እስረኞች ላይ ለማስተላለፍ በተደረገው መመካከር ማንን በእስር እናስቀር ማንን እንፍታ በሚለው ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ክርክር ተደርጎ እንደነበር ታውቋል:: ክርክሩ ያተኮረው በእስር ከሚገኙት መሃል ቢፈቱም ችግር በማይፈጥሩት ላይ እናተኩር ወይም ከትልልቆቹ የቅንጅት መሪዎች መሃል አንድ ሁለቱን እንቀላቅል በሚለው ጉዳይ ላይ

እንደነበር ታውቋል:: በነበረው ውይይት ላይ በመጪው ሰኞ እለት ምንም አይነት የብይን ውሳኔ እንዳይሰጥ የሚለው ሃሳብ በስምምነት ያለፈ ሲሆን ይህ ውሳኔ ለዳኞቹም እንደተነገራቸው ታውቋል:: በሃገራችን ፍትህ እንዲህ በጫትና በኮኛክ በደነዘዙ ህሊናዎች እጅ መውደቋ የሚያስተዛዝብ ሆኗል::

## የቅንጅት ለአንድትና ለዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ የጠራውን የትግል ጥሪ አደሰ

«ለቆሙለት መሪዎቹ ያልቆመ፡ ለተሟገቱለት ያልተሟገተ፤ ለተንገላቱለት ያልተንገላታ ህዝብ የመጨረሻው እድሉ መሪ አልባ መሆን ነው» በሚል ሰሜት ከሃገር ውጭ የሚኖረው ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በአለም ዙሪያ የሚያደርገውን «የፖለቲካ መሪዎቻችን ጋዜጠኞቻችን፣ የመብታችን ተሟጋቾችና አስተማሪዎቻችን ይፈቱ የሚል እንቅስቃሴ፤ የሃገራችን ህዝብ በመደገፍ የራሱን ድርሻ እንዲያበረክት ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ያደረገውን ጥሪ በትናንቱ እለት አንደገና አድሶታል:: ይህንን በቅንጅት የተጠራው የትምህርት ማቆም፣ በስራ ቦታ ላይ የመለገም የመዝናኛ ቦታዎችን ጎዳናዎችን ጭር በማድረግ በጸሎትና በምልጃ የታጀበውን የህዝብ የትግል ጥሪ የሚደግፉ ፖለቲካና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አባላቶቻቸውንና ደጋፊወቻቸውን ለትግሉ ተሳታፊ ለማድርግ ዝግጅቶች እያደረጉ እንደሆነ ተገልጧል::

በሌላ በኩልም ህዝብ የሰላማዊ ሰልፍ የማድርግ መብቱ በተገፈፈበት፣ ፍርድ ቤቶች ከጠቅላይ ሚኒስተሩ ትእዛዝ እተየቀበሉ በሚበይኑበት፣ የህገሪቱ የመገኛኛ ብዙሃን ሙሉ በሙሉ በገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ስር በወደቀበት፣ ሌላው ቀርቶ በኢንተር ኔት የሚጠቀም ዜጋ በሚገባባቸው ሱቆች ስሙና አድራሻው እንዲመዘገብ ደንብ የሚያወጣ መንግስት በላበት ሃገር፤ ገዥው ፓርቲ እንዳሻው በገፍ እንዲያስር በገፍ እንዲገድል ትእዛዝ ሲሰጠው እሺ ብሎ የሚፈጽም፣ በገዥው ፓርቲ እምቢተኛነት የተነሳ ህገመንግስታዊ ነጻነት እንዲያጣ የተደረገ የጦር፣ የስላላና የፖሊስ ሃይል ባለበት ሃገር እራሳቸውን ተቃዋሚ አድርገው በወያኔ ፓርላማ ውስጥ የገቡ የፓርላማ አባላት ሌላው ቀርቶ ወያኔ ለፈረንጆቹ መሸወጃ ሲል መለስ ዜናዊ በፓርላማ ውስጥ የፈቀደውን ነገር ግን የፓርላማ አባላቱ የመረጣቸው ህዝብ በየመንደሩ ያጣውን የመናገር መብት በመጠቀም የሃገሪቱን የህሊና እስረኞች ጉዳይ ዋና አጀንዳቸው አድርገው እንዲያነሱ ጥያቄ ቀርቧል:: ይህን ጥያቄ ያቀረበው «በኢትዮጵያ የዳቦ ጥያቄ ምላሽ ከዴሞክራሲ ጥያቄ ምላሽ ጋር የተሳሰረ ነው» የሚል መግለጫ ያወጣው «ልማት በነጻነት» በሚል እራሱን ያስተዋወቀው የኢትየጵያውያን ኔት ወረክ ቡድን ነው:: ይህ መግለጫ ተቃዋሚ ነን የሚሉ የፓርላማ አባላት እራሳቸውን ከታሪክ ተወቃሽነት ማዳን የሚችሉት ፓርላማ የገቡበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን እንደ የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በህሊናቸው በመመራትና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሃገርንና ወገን አስቀድመው ድምጻቸውን በማሰማት ብቻ እንደሆነ አትቶበታል::